## የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኤርትራ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ በአሁን ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ አቋም ፡

በፌዴራሲዮኑ ፡ ዘመን ፡[1] በኤርትራ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ከታወጁት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ሕግጋት ፡ አንዱ ፡ የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ነው ።[2] ይህ ፡ አዋጅ ፡ ከኢጣሊያን ፡ የቅኝ ፡ አገዛዝ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ የነበሩትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋትን ፡ በመተካት ፤[3] ሰፋ ፡ ያለ ፡ መሠረታዊ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ደረጃ ንና ፡ እነዚህን ፡ ሁኔታዎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውል ፡ የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ መቆጣጠሪያ ፡ ድርጅት ፡ መሥርቶ ፡ ስለ ፡ አሠሪዎች ፡ ማሕበሮችና ፡ ስለሠራተኛ ፡ ማኅበሮች ፡ አመዘጋገብ ፡ ደነገገ ።

ይህ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ከሌላ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ተመሳሳይ ፡ ሕግጋት ፡ የአያሌ ፡ ዓመታት ፡ ቅድሚያ ፡ ነበረው ። ከኤርትራ ፡ ውጭ ፡ መሠረታዊ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎችን ፡ የወሰነ ፡ የመጀመሪያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ፡ ነው ፤[4] ምናልባትም ፡ የ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲ ፡[5] እስከወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ኤርትራ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ሠራተኞችን ፡ የሚደግፉ ፡ መሠረታ ውያን ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት ፡ በሙሉ ፡ አልተወሰኑም ፡ ነበር ።[6] ከኤርትራ ፡ ውጭ ፡ ያሉትን ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበሮች ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡

---

1. ከ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከብሪታንያ ፡ ወታደራዊ ፡ (ሚሊተሪ) ፡ አስተዳደር ፡ ፍጻሜ ፡ ጀምሮ ፡ ኤርትራ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ ጋር ፡ እስከ፡ተዋሐደችበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የበላይ ፡ ገዥነት ፡ ሥር ፡ የውስጥ ፡ አስተዳደር ፡ እያላት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋር ፡ በፌዴራሲዮን ፡ ተያይዛ ፡ ነበር ። በፌዴራሲዮን ፡ ዘመንና ፡ ከዚያ ፡ በኋላም ፡ ስለኤርትራ ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ ዘርአብሩክ ፡ አበራ ፡ የጻፈውን ፡ "ዘ፡ሊጋል ፡ ስታተስ ፡ ኦቭ ፡ ኤርትሪያ" ፡ የሚል ፡ ማቲሪያልስ ፡ ፎር፡ ፐብሊክ ፡ ሎው ፡ ቱ ፡ ፲፱፻፷፩-፲፱፻፷፮ ፡ (በኬ ፡ ሬደን ፡ የተዘጋጀ ፡ ያልታተመ ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ ቤተ፤ መጻሕፍት ፡ ፲፱፻፷፮) ፡ ውስጥ ፡ ይመለከቷል ።
2. የኤርትራ ፡ ጋዜጣ ፤ ቮልዩም ፡ ፳ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡
3. በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የተጻፉትን ፡ ሕግጋት ፡ የሚዘረዘረውን ፡ የአዋጁን ፡ ሠንጠረዥ ፡ ሁለት ፡ ይመለከቷል ።
4. የፋብሪካ ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፵፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፶፰ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲ተኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፳ ፡ የንግድና ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስትርን ፡ በፋብሪካ ፡ ውስጥ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ እንዲያወጣ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቶት ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሥልጣን ፡ በፍጹም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አልዋለም ። ጄ ፡ ቮን ፡ ባውዲሲን ፡ "ስለተግባረ — ሥራ ፡ መሪ ፡ አሳብ ፡ (ፖሊሲ) ፡ መነሻ ፡ ንድፍ ፤" የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ሁለት ፡ ገጽ ፡ ፹፮ ፤ ፹፱ ፡ (፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም) ። ሚኒስትሩ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ላይ፡ ለመጨመርና፡ ያሉትንም፡ ለማሻሻል፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ይህን ፡ የመሰሉ ፡ ደንቦችን ፡ ሲያወጣ ፡ ይህን ፡ ያደረገው ፡ በ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ መሠረት ፡ እንጂ ፡ በፋብሪካ ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ አይደለም ። የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፫፶፪ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፬ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፳ን ፡ ይመለከቷል ።
5. ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፬ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፳ ።
6. አንዳንድ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ደንቦች ፡ ከሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ተነፃፃሪ ፡ ደንቦች ፡ ለሠራተኞች ፡ የተሻሉ ፡ ነበሩ ፤ ለምሳሌ ፡ የዓመት ፡ የዕረፍት ፡ ፈቃድን ፡ ከነደመወዝ ፡ የሚመለከቱት ፡ ደንቦች ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪ሺ፭፻፷፪ን ፡ ከሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፳፪፡ ጋር ፡ ያነፃጽሯል ። ነገር ፡ ግን ፡ እያንዳንዱ ፡ ሕግ ፡ በሙሉ ፡ ሲወሰድ ፤ በይበልጥ ፡ ዝርዝር ፡ በመስጠቱና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ያልተመለከታቸውን ፡ ጉዳዮች ፡ በመመልከቱ ፡ ረገድ ፡ የሠራተኛ ፡ አዋጅ ፡ ከሁለቱ ፡ የተሻለ ፡ ይመስላል ።

የጠቀሰ ፡ ሕግ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ነው ፤[7] ደግሞም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት፡ በሙሉ ፡ የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ መቆጣጠሪያ ፡ ድርጅት ፤[8] የተመሠረተው ፡ በ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ መቆጣጠሪያ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መቋቋም ፡ በወጣው፡ አዋጅና ፤[9] በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ደረጃ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ነው ።[10]

ሆኖም ፡ ቢያንስ ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኤርትራ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ፡ የወጡትን ፡ ጉዳዮች ፡ የሚመለከቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠቅላላ ፡ ሕግጋት ፡ ነበሩ ። የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዓላማ ፡ እነዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግጋትና ፡ የፌዴራሲዮኑ ፡ ፍጻሜ ፡ በተባለው የሠራተኛ፡አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ላይ፡ያስከተሉትን ፡ ሕጋዊ፡ውጤት ፡ ለመመርመር ፡ነው፤ ማለትም ፡ አዋጁ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ሕጋዊ ፡ ጽኑነት ፡ እንዳለው ፡ ሕጋዊ ፡ ጽኑ ነት ፡ ካለውም ፡ ጽኑነቱ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ይህ ፡ ጥያቄ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የጋራ ፡ መብት - ነክ ፡ ሕግ ፡ በጠቅላላው ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ ጭብጦችን ፡ ያነሳል ። በተጨማሪ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ የአሠሪዎችና ፡ የሠራተኞች ፡ መብቶ ችንና ፡ ግዴታዎችን ፡ ይመለከታል ።

አንድ ፡ ምሳሌ ፡ ብቻ ፡ ለመውሰድ ፡ ያህል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግና ፡ የኤርትራ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ ከደመወዝ ፡ ጋር የሚሰጥ ፡ ፈቃድን ፡ በሚመለከቱ ፡ ደንቦቻቸው ፡ ይለያያሉ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ለሠራተኞች ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ፈቃድ ፡ ከግማሽ ፡ ደሞዝ ፡ ጋር ፡ ሲሰጣቸው ፤[11] የሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ለሠራተኞች ፡ በሕ መም ፡ ምክንያት ፡ ፈቃድ ፡ ከደመወዝ ፡ ጋር ፡ እንዲሰጥ ፡ በፍጹም ፡ አይደነግግም ። ከሥራውም ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ የቀረ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ስለአለ ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ሠራተኛው ፡ ለቀረበት ፡ ጊዜ ፡ አሠሪው ፡ ለሠራተኛው ፡ ያለበት ፡ ደመወዝ ፡ የመክፈል ፡ ግዴታ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ በሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ፡ ሊገለጽ ፡ ይችላል ፡ ግን ፡ ጉዳዩ ፡ በሁለቱም ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ሊገለጽ ፡ አይችልም ።

---

7. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፬፻፮ ፡ (፪) ን ፡ (የሠራተኞች ፡ ማኅበሮች ፡ መመዝገብ) ፡ እና ፡ ቍጥር ፡ ፳፭፻፲፩፻፳፫ ፡ (በአሠሪዎችና ፡ በሠራተኞች ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ የኅብረት ፡ ስምምነቶች) ፡ ይመለከ ቷል ።
8. በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቍ. ፬ የተጠቀሰው ፡ የፋብሪካ ፡ አዋጅ፡ ስለፋብሪካ ፡ መርማሪ ፡ አሺሺም ፡ ደነ ገገ ፡ ግን ፡ የፋብሪካ ፡ ምርመራ ፡ ቅንጅት ፡ በዚያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋለ ፡ አይመስልም።
9. ትዕዛዝ ፡ ቍጥር ፡ ፴፮ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፬ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፬ ።
10. አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፴፪ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ።
11. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪ሺ፭፻፴፪ ።
12. የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፳፬ ፡ (፫) ፡ አንድ ፡ ሠራተኛ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ለገሚስ ፡ ጊዜ ፡ በአደጋ ፡ ወይም ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ ቢቀር ፡ ሠራተኛው ፡ የሙሉ ፡ ቀን ፡ ደመወዝ ፡ እንዲያገኝ ፡ መብት ፡ ይሰጠዋል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሠራተኛው ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ ሙሉ ፡ የሥራ ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ቢቀር ፡ ከደመወዝ ፡ ጋር ፡ ስለሚሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ የሚናገር ፡ ደንብ ፡ በአዋጁ፡ ውስጥ ፡ የለም ። የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፳፭ን ፡ ይመለከቷል ።
   በሕመም ፡ ምክንያት ፡ ከደመወዝ ፡ ጋር ፡ የሚሰጥ ፡ ፈቃድን ፡ የሚመለከቱት ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ፡ አሠሪውን ፡ በተለየ ፡ ሁኔታ ፡ ማለት ፡ ሠራተኛው ፡ በሥራው ፡ ምክንያት ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ሕመም ፡ ሲደርስበት ፡ አላፊ ፡ ከሚያደርጉት ፡ ደንቦች ፡ መለየት ፡ አለባቸው ። በፍትሐ ፡ ብሔር ሕግና ፡ በሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ የአሠሪው ፡ አላፊነት ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ሁኔታ ያልተገኘ ፡ ደመወዝ ፡ መተካትን ፡ ይጨምራል ፡ የሁለቱ ፡ ሕግጋት ፡ ደንቦች ፡ ይለያያሉ ፤ ከሁለቱ ፡ አንዱ ፡ የተሻለ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ የያንዳንዱን ፡ ጉዳይ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በመመልከት ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ፪ሺ፭፻፶፯-፪ሺ፭፻፶፰ን ፡ ከሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፵፬ ፡ እስከ፡ ፵፮ ፡ ጋር ፡ ያነፃፅራል ።

## <u>የሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ በፌዴራሲዮኑ ፡ ዘመን ፡ ፲፱፻፶—፲፱፻፶፬</u>

ፌዴራሲዮኑ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ በሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ የወጡትን ፡ ጉዳዮች ፡ በከፊል ፡ የሚመለከቱ ፡ ሁለት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግጋት ፡ ታውጀው ፡ ነበር ፤ እነርሱም ፡ የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግና ፡ የ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የአሠሪና ፡ የሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ድንጋጌ ፡ ናቸው ።[13] ሁለቱም ፡ ሕግጋት ፡ ሰፊ ፡ የሕግ ፡ መሻሪያ ፡ ደንቦችን ፡ ይዘዋል ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ "በዚህ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ ተጽፈው ፡ ይሠራባቸው ፡ የነበሩት (ን) ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡" ሽሮአቸዋል ።[14] ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣውም ፡ አዋጅ ፡ በተመሳሳይ ፡ አነጋገር ፡ "በዚሁ ፡ ድንጋጌ ፡ ስለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ---- ከዚህ ፡ በፊት ፡ ሲሠራባቸው ፡ የቆዩት (ን) ሕጎች ፡ ደንቦች ፡ ወይም ፡ ትዕዛዞች" ፡ ሽሮአቸዋል ። በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ በድንጋጌው ፡ ስለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ሲሠራባቸው ፡ የቆዩት ፡ ሕግጋት ፡ ሁሉ ፡ <u>የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግና ፡ ድንጋጌው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በሚውሉበት ፡ ቦታ ፡ በነዚህ</u> ደንቦች ፡ ተሽረዋል ። ሆኖም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩም ፡ ሕግ ፡ ሆነ ፡ ድንጋጌው ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ አልነበረውም ።

በፌዴራሲዮኑ ፡ ዘመን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት ፡ ሕግጋት ፡ በግዛታዊ ፡ ተፈጻሚነታቸው ፡ ረገድ ፡ በሦስት ፡ ክፍሎች ፡ የሚመደቡ ፡ ነበሩ ። በኢትዮጵያና ፡ በኤርትራ ፡ ተፈጻሚነት ፡ የነበራቸው ፡ የፌዴራል ፡ ሕግጋት ፡ ነበሩ ፤ በፌዴራል ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡[16] መሠረት ፡ የፌዴራል ፡ ሕግጋት ፡ ተፈጻሚነት ፡ በመከላከያ ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ከውጭ ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ የሚደረግ ፡ ንግድና ፡ በኢትዮጵያና ፡ በኤርትራ ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ንግድ ፡ በመሳሰሉት ፡ በተለይ ፡ በተሰየሙ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ የተወሰነ ፡ ነበር ። ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ በኤርትራ ፡ ሳይሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ ተፈጻሚነት ፡ የነበራቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግጋትና ፡ በኤርትራ ፡ ብቻ ፡ ተፈጻሚነት ፡ የነበራቸው ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ ነበሩ ።

የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግና ፡ ስለ ፡ አሠሪና፡ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ ድንጋጌ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግጋት ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የሚመደቡ ፡ ነበሩ ፤ በሕጋዊ ፡ አስተሳሰብ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩም ፡ ሕግ ፡ ሆነ ፡ ድንጋጌው ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ተፈጻሚነት ፡ አል

---

13. ድንጋጌ ፡ ቍጥር ፡ ፵፱ ፡ <u>ነጋሪት ፡ ጋዜጣ</u> ፤ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፲፰ ።
14. ቍጥር ፡ ፫ሺ፫፻፵፯ ። የሚከተሉት ፡ ቍጥሮች ፡ ይህን ፡ አጠቃላይ ፡ የመሻሪያ ፡ ደንብ ፡ ያሻሽሉታል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ መሻሻያዎቹ ፡ ለዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ አግባብ ፡ የላቸውም ።
15. አንቀጽ ፡ ፴፯ ።
16. በአራቱ ፡ ኃያላን ፡ መንግሥታት ፡ (የተባበረው ፡ የአሜሪካን ፡ መንግሥት ፡ ታላቋ ፡ ብሪታንያ ፡ የሶቪየት ፡ ሕብረትና ፡ ፈረንሣይ) ፡ እና ፡ በኢጣሊያን ፡ መካከል ፡ በተደረገው ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ የቀድሞ ፡ የኢጣሊያን ፡ ቅኝ ፡ ግዛት ፡ የነበረችው ፡ የኤርትራ ፡ የወደፊት ፡ ዕድል ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ በሚሰጠው ፡ ምክር ፡ መሠረት ፡ እንዲወሰን ፡ ተደረገ ። የሰላም ፡ ውል ፡ ተቀጥላ ፡ (አኔክስ) ፡ ፲፩ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ በኤን ፡ ማርያን ፡ <u>በዘ ፡ ኢትዮፕያን ፡ ኤምፓየር ፡ ፌዴሬሽን ፡ ኤንድ ፡ ሎውስ</u> ፡ (ሮተርዳም ፡ ፲፱፻፷፬) ፡ ውስጥ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፶፬ ፡ የተጠቀሰ ። የፌዴራሉ ፡ አዋጅ ፡ ታህሣሥ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ ከተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ውስጥ ፡ የመጀመሪያዎቹን ፡ ሰባት ፡ አናቅጽ ፡ የያዘ ፡ ነበር ፤ ውሳኔውም ፡ ኤርትራ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋር ፡ በፌዴራሲዮን ፡ መልክ ፡ እንድትቀላቀል ፡ የቀረበውን ፡ አሳብ ፡ የሚመለከት ፡ ነበር ። የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ፌዴራሲዮኑን ፡ እንዲፈቅድ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እነዚህን ፡ ደንቦች ፡ ማጽደቅ ፡ ነበረባት ። ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፫፻፶፮ ። የፌዴራሉም ፡ አዋጅ ፡ ሆነ ፡ የአዋጁ ፡ ማጽደቂያ ፡ <u>በነጋሪት ፡ ጋዜጣ</u> ፡ ውስጥ ፡ አልታተመም ፤ ግን ፡ መጽደቁ ፡ በትዕዛዝ ፡ ቍጥር ፡ ፮ ፡ <u>ነጋሪት ፡ ጋዜጣ</u> ፤ ፲፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ ተጠቅሷል ። የፌዴራል ፡ አዋጁ ፡ ቃልም ፡ በማሪየን ፡ መጽሐፍ ፡ ተቀጥላ ፡ (አፔንዲክስ) ፡ ፪ ፡ ውስጥ ፡ ሊገኝ ፡ ይችላል ።

ነበራቸውም ። የፌዴራል ፡ ተፈጻሚነት ፡ ከነበራቸው ፡ ሕግጋትም ፡ ውስጥ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅን ፡ ይሽራል ፡ ወይም ፡ ያሻሽላል ፡ ተብሎ ፡ ሊተረጎም ፡ የሚችል ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። ስለዚህ፡ የሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ቢያንስ ፡ ፌዴራሲዮኑ፡ እስኪፈጸም፡ድረስ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ በሙሉ ፡ ጸንቶ፡ ቆይቷል

## የፌዴራሲዮኑ ፡ ፍጻሜ ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ከጸና ፡ ከአምስት ፡ ሳምንታት ፡ በኋላ ፡ ፌዴራሲዮኑ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ትዕዛዝ ፡ አማካይነት ፡ ተፈጸሞ ፡[17] ኤርትራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ ክፍል ፡ ሆነች ። የንጉሠ ፡ ነገሥቱና የኢትዮጵያ ፡ ፓርላሜንት ፡ የአጋጊነት ፡ ሥልጣን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ግዛት ፡ በሙሉ ፡ አጠቃለለ ፡ የወደፊት ፡ ግብራቸውም ፡ እንደሌላው ፡ ሥፍራ ፡ በኤርትራም ፡ተፈጻሚነት ፡ የሚኖረው ፡ ሆነ ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የነበሩት ፡ ሕግጋት ፡ ማለት ፡ በቀድሞው ፡ ፌዴራሲዮን ፡ ዘመን ፡ ለአንድ ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ተፈጻሚነት ፡ የነበራቸው፡ ሕግጋት ፡ ምን ፡ ሆኑ ?

ፌዴራሲዮኑን ፡ የሻረው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ትእዛዝ ፡ ይህን ፡ ጥያቄ ፡ በግልጽ ተመልክቶታል ። ትዕዛዙ ፡ ሲተረጎም ፡ የቀድሞው ፡ ሁኔታ ፡ አለአንዳች ፡ ለውጥ ፡ እንዲጠበቅ ፡ አድርጓል ። ጸንተው ፡ የቆዩት ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ ተፈጻሚነታቸው፡ እንዲቀጥል ፡ ተደርጓል ፡ ከዚህም ፡ በማያያዝ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በትዕዛዙ ፡ በቀጥታ፡ ባይገለጽ ፡ ጸንተው ፡ የቆዩት ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ የሚመለከቱትን ፡ ጉዳዮች ፡ የሚመለከቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግጋት ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዳይኖራቸው ፡ ተደርጓል ። ይህን ፡ ውጤት ፡ ያስከተለው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ለተመለከተው፡የትዕዛዙ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ እና ፡ ፪ ፡[18] የተሰጠ ፡ ሰፊ ፡ ትርጓሜ ፡ ነው ፡

> "፩- ፡ ማናቸውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ድርጅት ፡ በሕግ ፡ በትዕዛዝ ፡ በውል ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ የተፈቀደለት ፡ የተሰጡት ፡ ወይም ፡ ያገኛቸው ፡ ማናቸውም ፡ መብቶች ፡ ከግዴታዎች ፡ ነጻ ፡ የሚያደርጉ ፡ መብቶች ፡ ኮንሴሲዮኖችና ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፡ እንዲሁም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ የማግኘት ፡ ባለቤት ፡ የመሆን ፡ ባለቤትነትን ፡ የማስተላለፍ ፡ መብቶች ፡ ጭምር ፡ እንዳሉ ፡ በሙሉ ፡ ጸንተው ፡ ይቀጥላሉ ።
> ፪- በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ጸንተው ፡ የሚሠራባቸው ፡ ወይም ፡ የፌዴራል ፡ አቋም ፡ በመኖሩ ፡ ምክንያት ፡ የወጡት ፡ ሕጎች ፡ አዋጆችና ፡ ደንቦች ፡ በሙሉ ፡ ሆነ ፡ በከፊል ፡ ለአስተዳደሩ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠራባቸው ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ሁሉ ፡ ወደፊት ፡ በሚወጡ ፡ ሕጎች ፡ ተሠርዘው ፡ እስኪተኩ ፡ ድረስ ፡ እንዳሉ ፡ ጸንተው ፡ የሚሠራባቸው ፡ ይሆናሉ ። ያሉትም ፡ የአስተዳደር ፡ ድርጅቶች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ሆነው ፡ እነዚሁኑ ፡ ሕጎች ፡ በሥራ ፡ ላይ መዋላቸውን ፡ እንዲቀጥሉ ፡ ያደርጋሉ ።"

17. ትዕዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯ ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፫ ።
18. በቁጥሮች ፡ ፩ ፡ እና ፡ ፪ ፡ ከመሻር ፡ ያልዳኑትን ፡ አንዳንድ ፡ ዓይነት ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ የትዕዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ ያጸናል ፡ ብሎ ፡ ለመተርጐም ፡ ይቻላል ። ቁጥር ፡ ፩ ፡ "የቀድሞው ፡ የኤርትራ ፡ አስተዳደር ፡ መብቶች ፡ ሥልጣኖች ፡ ተግባሮችና ፡ ግዴታዎች ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ --- የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ መብቶች ፡ ሥልጣኖች ፡ ተግባሮችና ፡ ግዴታዎች ፡ ሆነዋል ፡" ብሎ ፡ ይደነግጋል ።

አንቀጽ ፡ ፩ ፡ እና ፡ ፯ ፡ የኤርትራን ፡ ሕግጋት ፡ ለማናቸውም ፡ ሰው ፡ መብት ፡ እስከሰጡ ፡ ድረስ ፡ ወይም ፡ "ለአስተዳደር ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠራባቸው" ፡ እስከማስፈለጋቸው ፡ ድረስ ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዲኖራቸው ፡ አድርጎአቸዋል ። ሁለቱም ፡ አናቅጽ ፡ በጣም ፡ የሚለያዩ ፡ ትርጉሞች ፡ ሊሰጡአቸው ፡ ይቻላል ። ለምሳሌ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ የተወሰኑ ፡ ሰዎች[19] ትእዛዙ ፡ እስከወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የአገኟቸውን ፡ መብቶች ፡ በመጠበቅ ፡ ሊወሰን ፡ ይችላል ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፌዴራሲዮኑ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ የነበሩትን ፡ ሕግጋት ፡ በመጥቀስ ፡ ከፌዴራሲዮኑ ፡ ፍጻሜ ፡ በኋላ ፡ ሊጠቀምባቸው ፡ ይቻላል ፡ የሚል ፡ ትርጉም ፡ ሊሰጠው ፡ ይችላል ። በሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ሲሆን ፡ የመጀመሪያው ፡ አተረጓጎም ፡ ቢበዛ ፡ የአዋጁን ፡ መሠረታዊ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ደንቦች ፡ ከፌዴራሲዮኑ ፡ ፍጻሜ ፡ ጀምሮ ፡ ደንቦቹ ፡ ለሚመለከቱአቸው ፡ ሰዎች ፡ ይጠብቅላቸዋል ፡ ሁለተኛው ፡ አተረጓጎም ፡ ደንቦችን ፡ ለወደፊት ፡ ሊጠቀምባቸው ፡ ለሚፈልግ ፡ ለማናቸውም ሰው ፡ በሙሉ ፡ ጽኑነታቸውን ፡ ይጠብቅለታል ። በተግባር ፡ ላይ ፡ ትዕዛዙ ፡ ይሠራባቸው ፡ የነበሩትን ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ ሁሉ ፡ ያጠቃልላል ፡ ተብሎ ፡ በሰፊው ፡ ተተርጉሟል ። የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅና ፡ ልክ ፡ ፌዴራሲዮኑ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ ፌዴራሲዮኑ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላም ፡ ሕጋዊ ፡ ጽኑነታቸውን ፡ እንደያዙ ፡ ቆይተዋል ።

## <u>የሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ከፌዴራሲዮኑ ፡ ፍጻሜ ፡ ወዲህ ።</u>

አሁን ፡ ከ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኋላ ፡ የወጡት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግጋት ፡ በሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ላይ ፡ ያስከተሉትን ፡ ውጤት ፡ መመርመር ፡ አለብን ። ፌዴራሲዮኑን ፡ የሻረው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ትዕዛዝ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ይሠራባቸው የነበሩትን ፡ አብዛኞቹን ፡ ወይንም ፡ ሁሉንም ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ በኤርትራ ፡ የውስጥ ፡ አስተዳደር ፡ አቋም ፡ መፍረስ ፡ ምክንያት ፡ እንዳይሻሩ ፡ አድርጎአል ። ነገር ፡ ግን ፡ ትዕዛዙ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋትን ፡ ከፌዴራሲዮኑ ፡ መንግሥት ፡ መፍረስ ፡ በኋላ ፡ በወጡት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግጋት ፡ ከመሻር ፡ ወይንም ፡ ከመሻሻል ፡ አይጠብቃቸውም ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ በሆነ ፡ መንገድም ፡ ሊጠብቃቸው ፡ አይችልም ።

ከፌዴራሲዮኑ ፡ ፍጻሜ ፡ ወዲህ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞችን ፡ ከሚመለከቱት ፡ ሕግጋት ፡ ሌላ ፡ ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ አራት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ሕግጋት ፡ ወጥተዋል ፤ እነዚህም ፡ በ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡[20] በ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ መቆጣጠሪያ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት መቋቋም ፡ የወጣ ፡ ትእዛዝ ፡ በ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ደረጃ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ እና ፡ የ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፪ ፡ ናቸው ። የተዋሐደው ፡ ውጤታቸው ፡ የኤርትራውን ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ በሙሉ፡ ሳይሆን ፡ በከፊል ፡ የሻረ ፡ ይመስላል ።

ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ ድንጋጌ ፡ ፓርላሜንቱ ፡ ባልተሰበሰበበት ፡ ጊዜ ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ መሠረት ፡ በንጉሠ ፡ ነገ

19. ለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የመሻሪያ ፡ ደንቦች ፡ አፈጻጸም ፡ ሲባል ፡ ሕጉ ፡ ሲወጣ ፡ በተፈጸሙ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎችና ፡ ባልተፈጸሙ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎች ፡ መካከል ፡ ልዩነትን ፡ የሚፈጥሩትን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፫ሺ፫፻፵፰ን ፡ እና ፡ ፫ሺ፫፻፵፱ን ፡ ያነፃፅሯል ።

20. አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፫ ።

ሥቱ ፡ ታወጀ ።[21] አንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ እንደሚያዘው ፡ ድንጋጌው ፡ ለሚቀጥለው ፡ የፓርላ ሜንቱ ፡ ስብሰባ ፡ ቀርቦ ፡ ፓርላሜንቱም ፡ አንዳንድ ፡ ማሻሻያዎችን ፡ በመጨመር ፡ ተቀብሎ ፡ አጸደቀው ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ሕጉ ፡ እንደ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የአሠሪና ፡ ሠራ ተኛ ፡ ጉዳይ ፡ አዋጅ ፡ እንደገና ፡ ወጣ ።

ይህ ፡ ሕጉን ፡ እንደገና ፡ እንደማውጣት ፡ የሚቆጠር ፡ ነበር ፡ በፊት ፡ የ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድንጋጌ ፡ የነበረው ፡ የ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ሆነ ። የዚህ ፡ ለውጥ ፡ ውጤት በሕጉ ፡ አርእስት ፡ መለወጥና ፡ በተደረጉት ፡ ንዑሳን ፡ ማሻሻያዎች ፡ የሚወሰን ፡ አይ ደለም ። ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደተመለከትነው ፡ ድንጋጌው ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሲወጣ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ተፈጻሚነት ፡ አልነበረውም ፡ ስለዚህም ፡ የመሻሪያ ፡ ደንቦች ፡ በኤርትራ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት ፡ አልነበራቸውም ። ሆኖም ፡ ሕጉ ፡ እንደገና ፡ በአዋጅ ፡ መልክ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ ፌዴራሲዮኑ ፡ ስለ ተፈጸመ ፡ አዋጁ ፡ እንደ ፡ ድንጋጌው ፡ ሳይሆን ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት ፡ በሙሉ ፡ የጸና ፡ ሆነ ። የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅን ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ያልተመለከቱት ፡ የመሻሪያ ፡ ደንቦች ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ላይ ፡ ተፈጻ ሚነትን ፡ አገኙ ፡ ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀ ሱትን ፡ ጉዳዮች ፡ የሚመለከቱ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ደንቦችም ፡ በተለ ይም ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበሮችንና ፡ የአሠሪዎች ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመለከቱት፡ደንቦች፤[22] በተባለው ፡ አዋጅ ፡ ተሻሩ ።

የሕጉ ፡ ከፌዴራሲዮኑ ፡ ፍጻሜ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ መውጣት ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እንደሚያስከትል ፡ ግልጽ ፡ ይመስላል ። ምናልባት ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ግልጽ ፡ መስሎ የማይታየው ፡ አንድ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ድንጋጌ፡ ንዑሳን ፡ ማሻሻያዎች ፡ ተጨምረ ውበት ፡ በፓርላሜንቱ ፡ ሲጸድቅ ፡ ሕጉ ፡ በጠቅላላው ፡ እንደገና ፡ እንደወጣ ፡ ሕግ ፡ሳይ ሆን ፡ ተሻሽሎ ፡ እንደወጣ ፡ ሕግ ፡ ለምን ፡ አይቆጠርም ፡ የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። ም ክንያቱ ፡ የሚገኘው ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ ድንጋጌ ፡ የማውጣት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ሥልጣንና ፡ በሌላው ፡ በኩል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ የሚካፈሉት ፡ አዋ ጆችን ፡ የማውጣት ፡ ሥልጣን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ንጉሠ ነገሥታዊ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለሚቀጥለው ፡ የፓርላሜንቱ ፡ ስብሰባ ፡ እንዲቀርቡ ፡ አን ቀጽ ፡ ፺፪ ፡ ያዛል ፡ ብለናል ። በአንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ መሠረት ፡ ፓርላሜንቱ ፡ ሊወስድ ፡ የሚ ችለው ፡ የሥራ ፡ እርምጃዎች ፡ ሁለት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ፓርላሜንቱ ፡ ድንጋጌውን ፡ ላይ ቀበለው ፡ ይችላል ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ድንጋጌው ፡ የጸና ፡ መሆኑ ፡ ይቀራል ።[23] በሌላው በኩል ፡ ፓርላሜንቱ ፡ ድንጋጌውን ፡ ሊቀበለው ፡ ይችላል ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ድንጋጌ ው ፡ <u>እንደ</u> ፡ ድንጋጌ ፡ እንደጸና ፡ ይቀራል ።[24] የፓርላሜንቱ ፡ አንድ ፡ ድንጋጌን ፡

21. "አማካሪዎች ፡ (የፓርላሜንት) ፡ ባልተሰበሰቡት ፡ ጊዜ ፡ የሚያስቸኩል ፡ ጉዳይ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ" ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ እንዲያውጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ ይፈቅድለታል ።

22. የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ቁጥሮች ፡ ፹፪ ፡ እስከ ፡ ፹፰ ፡ እና ፡ ፩፻ ፡ እስከ ፡ ፩፻፭ ። የሥራ ፡ ክርክ ሮች ፡ ውሳኔን ፡ የሚመለከቱት ፡ ቁጥሮች ፡ ፸፯ ፡ እስከ ፡ ፹፩ ፡ በአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ አዋጅ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የተሻሩ ፡ ይመስላሉ ።

23. ድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ ፵፩ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፲፱ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፩ ፡ የሰረዘውን ፡ የመሰ ረተ ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፩ን ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲ ፡ ይመለከቷል ። ድንጋጌ ፡ የተሰረዘበት ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ይመስላል ።

24. ለምሳሌ ፡ ድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ን ፡ ፲፱፻፶ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፯ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ ያጸደቀውን ፡ የማጽደቂያ ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፩ን ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፱ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፬ ፡ ይመለከቷል ። የማጽደቂያው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፰ ፡ ውስጥ ፡ ተጠቅሶአል ።

በሙሉ ፡ መቀበል ፡ ሕጉን ፡ እንደገና ፡ እንደማውጣት ፡ መቆጠሩ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ፡[25] ግን ፡ እንደዚህ ፡ መቆጠር ፡ የማይገባው ፡ ይመስላል ።

ነገር ፡ ግን ፡ የፓርላሜንቱ ፡ የሥራ ፡ እርምጃ ፡ ድንጋጌውን ፡ እንዳለ ፡ መቀበል ፡ ሳይሆን ፡ መሻሻያዎችን ፡ አክሎ ፡ መቀበል ፡ ከሆነስ ? በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ፓርላሜንቱ ፡ የሚሠራው ፡ የግድ ፡ በአንቀጽ ፡ ፹፰—፺ ፡ እንደተጻፈው ፡ አዋጅ ፡ በማውጣት ፡ ሥልጣኑ ፡ መሠረት ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ማሻሻያዎቹ ፡ ንዑሳን ፡ ሆኑም ፡ አልሆኑ ፡ የፓርላሜንቱ ፡ ድርጊት ፡ የድሮውን ፡ ድንጋጌ ፡ ለመተካት ፡ አዲስ ፡ አዋጅ ፡ እንደማውጣት ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ።[26]

ድንጋጌውን ፡ ከማሻሻያዎች ፡ ጋር ፡ በመቀበል ፡ እና ፡ እንዳለ ፡ በመቀበል ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ <u>በነጋሪት ፡ ጋዜጣ</u> ፡ ሲታተሙ ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ የሚሰጠው ፡ ቅጽ ፡ (ፎርም) ፡ ያስረዳል ። ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ የመግቢያው ፡ መግለጫና ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ሁለት ፡ አናቅጽ ፡ እንደሚከተለው ፡ ይነበባሉ ፡

> "ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ነሐሴ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በቁጥር ፡ ፵፱ ፡ ድንጋጌ ፡ የወጣ ፡ ስለሆነ ፤
>
> <u>ፓርላሜንቱም ፡ በድንጋጌው ፡ የማሻሻያ ፡ ሐሳብ ፡ አቅርቦ ፡ የተሻሻለውን ፡ ሕግ ፡ ያጸደቀው ፡ በመሆኑ ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችን ፡ በአንቀጽ ፡ ፴፩ ፡ እና ፡ ፹፰ ፡ የተጻፈውን ፡ ተመልክተን ፡</u>
>
> የሕግ ፡ መወሰኛና ፡ የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤቶቻችን ፡ መክረውበት ፡ ያቀረቡልንን ፡ ተቀብለንና ፡ ፈቅደን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ አውጀናል ።
>
> ፩/ ይህ ፡ አዋጅ ፡ የ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣ፡ አዋጅ ፡ ተብሎ ፡ ሊጠቀስ ፡ ይቻላል ።
>
> ፪/ ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ ቁጥር ፡ ፵፱ ፡ ድንጋጌ ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፲/፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሚል ፡ ተተክቶ ፡ <u>ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተሻሻለው ፡ መሠረት ፡ ሕግነቱ ፡ እንደጸና ፡ ቀጥሏል ።</u> (አንክሮው ፡ የተጨመረ ፡ ነው) ።

የመግቢያው ፡ መግለጫ ፡ የተሻሻለውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፹፰ ፡ መጥቀሱና ፡ ለሕጉ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩ ፡ አርእስት ፡ መሰጠቱ ፡ እንደሚያመለክቱት ፡ ሕጉ ፡ አዲስ ፡ አዋጅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከቀድሞ ፡ ድንጋጌ ፡ ጋር ፡ ሙሉ ፡በሙሉ ፡ የሚዛመድ ፡ አይደለም ። ደግሞም ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ እንደሚያመለክተው ፡ በፓርላሜንቱ ፡ ከተሻሻሉት ፡ ደንቦች ፡ በስተቀር፡አዋጁ፡የቀድሞውን ፡ ድንጋጌ፡በሙሉ ፡ እንደገና ፡ ያወጣዋል።

---

25. የአንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ ቋንቋ ፡ በሁለቱም ፡ መንገድ ፡ ያስኬዳል ። ይህ ፡ አንቀጽ ፡ ፓርላሜንቱ ፡ አንድ ፡ ድንጋጌን ፡ ሲያጸድቅ ፡ (፩) ፡ ድንጋጌው ፡ "እንደ ፡ ጸና ፡ ይቀራል" እና ፡ (፪) ፡ ድንጋጌው ፡ "መጽናቱም ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ መውጣት ፡ አለበት" ፡ ይላል ።

26. የዚህ ፡ ልዩነት ፡ አንዱ ፡ ውጤት ፡ የፓርላማው ፡ አንድ ፡ ድንጋጌን ፡ ከማሻሻያዎች ፡ ጋር ፡ ማጽደቅ ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፹፰ ፡ መሠረት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መቅረብ ፡ ሲገባው ፡ በአንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ መሠረት ፡ የተደረገ ፡ የፓርላሜንት ፡ ድንጋጌውን ፡ መቀበል ፡ ወይም ፡ አለመቀበል ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መቅረብ ፡ አያስፈልገውም ።

ይህ ፡ ቅጽ ፡ ፓርላሜንቱ ፡ ድንጋጌውን ፡ እንዳለ ፡ ሲያጸድቅ ፡ ከሚጠቀምበት ፡ ቅጽ ፡ ጋር ፡ ሊነፃፀር ፡ ይቻላል ፡ ለምሳሌም ፥ የ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ፡ ማጽደቂያ ፡[27] እንደሚከተለው ፡ ይነበባል ፥

"በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ መሠረት ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በቍጥር ፡ ፳፫ ፡ የወጣውን ፡ ድንጋጌ ፡ ፓርላሜንቱ ፡ እንዲያጠናው ፡ ቀርቦለት ፡ ይህንኑ ፡ ድንጋጌ ፡ የተቀበለው ፡ መሆኑን ፡ ፓርላሜንቱ ፡ ስላ ስታወቀ ፥ ስለ ፡ አውራ ፡ ጐዳናዎች ፡ ማደሻ ፡ የዓመት ፡ ወጭ ፡ በ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣውን ፡ አዋጅ ፡ ስለማሻሻል ፡ የወጣ ፡ የ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድን ጋጌ ፡ ሕግነቱ ፡ እንደጸና ፡ ቀጥሏል ።"

አሁን ፥ እላይ ፡ ወደተጠቀሱት ፡ ከ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኋላ ፡ ወደወጡት ፡ ሕግጋት ስንመለስ ፥ እነዚህ ፡ ሕግጋት ፡ ባንድነት ፡ ሲነበቡ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የተደነ ገገውን ፡ መሠረታዊ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፥[28] የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ላልተመለከታቸው ፡ ጉዳዮች ፡ መሠረታዊ ፡ ሁኔታዎችን ፡ መሥርተው ፥[29] የአሠሪና ፡ የሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ መቆጣጠሪያ ፡ ቅንጅትን ፡ ፈጥረው ፥[30] ተቆጣጣሪ ዎቹ ፡ ሥራቸውን ፡ በቅጡ ፡ እንዲያከናውኑ ፡ የሚያረጋግጡ ፡ እርምጃዎችን ፡ ወስደ ዋል ።[31] በዚህ ፡ ረገድ ፡ ከኤርትራ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ጋር ፡ ለመወዳ ደር ፡ ችለዋል ። ሆኖም ፥ በኤርትራ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ተመሳሳይ ፡ ጉዳዮችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ በሙሉ ፡ አልተሻሩም ።

እነዚህ ፡ ሕግጋት ፡ የሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ መቆጣጠሪያን ፡ የሚመለከቱትን ፡ የሠ ራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ደንቦችን ፡ የመሻር ፡ ውጤት ፡ ያስከተሉ ፡ ይመስላል ። እነዚህም ፡ ደንቦች ፡ ለኤርትራ ፡ የሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ተቆጣጣሪዎች ፡ ቅንጅትን ፡ የመ ሠረቱና ፡ የተቆጣጣሪዎቹን ፡ ሥራ ፡ ለማቃለል ፡ የታቀዱት ፡ ናቸው ።[32] ለኢትዮጵያ የሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ መቆጣጠሪያ ፡ ቅንጅትን ፡ የመሠረቱት ፡ ሕግጋት ፡ ከዚህ ፡ በፊት ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ ይመለከቱ ፡ የነበሩትን ፡ ሕግጋት ፡ ሁሉ ፡ ሽረዋል ፥[33] በነዚህም ፥

---

27. የማጽደቂያ ፣ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፣ ፩ ፥ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፱ኛ ፣ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፥ ድንጋጌ ፡ ቍጥር ፡ ፳፫ን ፡ ፲፱፻፶፱ ፥ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፯ኛ ፣ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ የጸደቀ ፡ ነው ።

28. ለምሳሌ ፥ በዓመት ፡ የዕረፍት ፣ ፈቃድ ፡ ረገድ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፣ ፪ሺ፭፻፷፪ ፡ መሠ ረት ፥ አራት ፡ የአገልግሎት ፣ ዓመታት ፣ ያለው ፡ ሠራተኛ ፣ በመደዳው ፡ የአሥር ፡ ቀናት ፡ የዓመት ፡ ዕረፍት ፣ ፈቃድ ፡ ከደመወዝ ፡ ጋራ ፡ ለማግኘት ፣ መብት ፡ አለው ፤ በሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር፡ ፫፻፪ ፡ አንቀጽ ፡ ፭ ፡ (፩) ፡ (ለ) ፡ መሠረት ፥ የአስራ ፡ ስድስት ፡ ቀናት ፡ የዕረፍት ፡ ፈቃድ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

29. ለምሳሌ ፥ ስለሞያ ፡ ሥራ ፡ መልመጃ ፡ ውሎች ፣ ከሚመለከቱት ፡ ጥቂት ፡ ልዩ ፣ ደንቦች ፡ (ቍጥሮች ፡ ፪ሺ፭፻፺፬ ፣ እስከ ፡ ፪ሺ፭፻፺፯) ፡ በስተቀር ፣ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፣ በወጣቶች ፡ አቀጣጠር ፡ ላይ ፡ ምን ም ፡ ወሰኖች ፣ አላደረገም ፡ አሁን ፣ የሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ደረጃ ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፫ ፡ ዕድሜው ፡ ከአሥራ ፡ አራት ፣ ዓመት ፣ በታች ፡ የሆነ ፡ ልጅ ፡ በኢንዱስትሪ ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፣ ውስጥ ፡ እንዳይ ቀጠር ፣ በጠቅላላው ፡ ይከለክላል ፥ ዕድሜው ፣ ከአሥራ ፡ አራት ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡የሆነ፡ ልጅም ፡ እንዲቀጠር ፡ የሚፈቀደው ፡ በተለዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ ብቻ ፡ ነው ።

30. አንቀጽ ፡ ፭ ፥ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ መቆጣጠሪያ ፣ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የወጣ ፣ ትዕዛዝ ።

31. አናቅጽ ፣ ፯ ፡ እና ፡ ፰ ፥ ስለ ፡ ሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ደረጃ ፣ የወጣ ፣ አዋጅ ።

32. አናቅጽ ፣ ፷፯ ፣ እስከ ፡ ፷፯ ፥ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ።

33. ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ መቆጣጠሪያ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መቋቋም ፡ የወጣው ፡ ትዕዛዝ ፡ ግልጽ፡ የመሻሪያ ፣ ደንብ ፡ አልያዘም ፥ ግን ፡ የአሠሪና ፡ የሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ መቆጣጠሪያን ፣ የመሠረተ ፡ ማን ኛውንም ፡ የቀድሞ ፡ ሕግ ፡ በስውር ፡ (በግልጽ ፡ ሳይነገር) ፡ ሽሯል ፡ ተብሎ ፣ ይገመታል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ስለሥራ ፡ ሁኔታዎች ፣ ደረጃ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ የመሻሪያ ፡ ደንብ ፡ "ከዚህ ፡ አዋጅ ፡ ውስጥ ፡ ስለተ መለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ከዚህ ፣ ቀደም ፡ ሲሠራባቸው ፡ የቆዩት ፡ --- ሕጐች ፡ (ን) ፣ ሁሉ ፡ " ፡ በግልጽ ፡ ሽሮአቸዋል ። (አንቀጽ ፡ ፪ ) ።

ሕግጋት ፡ ውስጥ ፡ የኤርትራን ፡ የሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ መቆጣጠሪያ ፡ ደንቦችን ፡ ከመ ሻር ፡ የሚያድን ፡ አንዳችም ፡ ነገር ፡ የለም ። አሁን ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ተፈጻሚነት ፡ ያለው ፡ ሕግ ፡ የኤርትራ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ሳይሆን የ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ መቆጣጠሪያ ፡ የወጣ ፡ ትዕዛዝና ፡ የ፲፱፻፵፫ ፡ ስለሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ደረጃ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ይመስላል ።

ሆኖም ፡ መሠረታዊ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎችን ፡ በሚመለከትበት ፡ መጠን ፡ የሠራ ተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ክፍሎች ፡ ሕጋዊ ፡ ጽኑነት ፡ የቀጠለ ፡ ይመ ስላል ። ለዚህም ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ አሉ ። አንደኛ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ቍጥር ፡ ፫፻፪ ፡ እና ፡ ስለሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ደረጃ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ለሠራተኞች ፡ ከሕጉ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያና ፡ ከአዋጁ ፡ የተሻሉ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎችን ፡ የሚመሠ ረቱ ፡ ማናቸውንም ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሕጋዊ ፡ ውሳኔ ፡ ከመሻር ፡ የሚያድኑ ፡ ደንቦ ችን ፡ ይዘዋል ።[34] አንዳንድ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ደንቦች ፡ ከኢትዮጵያ ሕግጋት ፡ ተመሳሳይ ፡ ደንቦች ፡ በይበልጥ ፡ የተሻሉ ፡ ናቸው ፡ እነዚህም ፡ የአዋጅ ፡ ደንቦች ፡ ከመሻር ፡ ድነዋል ።[35]

ሆኖም ፡ የትኞች ፡ የአዋጁ ፡ ደንቦች ፡ "በይበልጥ ፡ የተሻሉ" ፡ ከሚለው ፡ ደረጃ፡ ደርሰዋል ፡ ብሎ ፡ በትክክል ፡ መግለጽ ፡ ሳያስቸግር ፡ አይቀርም ። በመጀመሪያ ፡ ግን ኙነት ፡ ያላቸው ፡ ደንቦች ፡ ምን ፡ እንደሚያደርጉ ፡ መወሰን ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ይህን፡ ችግር ፡ በምሳሌ ፡ ለማስረዳት ፡ ከአዋጁ ፡ ደንቦች ፡ በይበልጥ ፡ ችግሩን ፡ የሚያመለክት፡ አንድ ፡ የፈጠራ ፡ ጉዳይ ፡ እንወስዳለን ። የሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ በቀን ፡ ዘጠኝ ፡ የሥራ ፡ ሰዓቶችና ፡ በሳምንት ፡ አምስት ፡ የሥራ ፡ ቀናት ፡ ደነገገ ፡ እንበል ፡ ግን ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፪ ፡ በቀን ፡ ስምንት ፡ የሥራ ፡ ሰዓቶ ችና ፡ በሳምንት ፡ ስድስት ፡ የሥራ ፡ ቀናት ፡ ደነገገ ፡ እንበል ። በ"ይበልጥ ፡ የተሻሉ" የሚለው ፡ ደረጃ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ተፈጻሚነት ፡ ቢኖረው ፡ በኤርትራ ፡ ያሉትን ፡ ሠራ ተኞች ፡ ከያንዳንዱ ፡ ደንቦች ፡ መደብ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥሩዎቹን ፡ ይፈቅድላቸዋል ፡ ይኸውም ፡ ከሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፪ ፡ ስምንት ፡ የሥራ ፡ ሰዓት ፡ በቀንና ፡ ከሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ አምስት ፡ የሥራ ፡ ቀናት ፡ በሳምንት ፡ ማለት ነው ። ውጤቱም ፡ በሳምንት ፡ አርባ ፡ የሥራ ፡ ሰዓት ፡ ብቻ ፡ ይወስንላቸዋል ፡ ይኸ ውም ፡ በማናቸውም ፡ ሕግ ፡ ከተደነገገው ፡ ያጠረ ፡ ይሆናል ።

ይህን ፡ የመሰለ ፡ ውጤት ፡ የአርቃቂዎችንም ፡ ሆነ ፡ የአጋጊዎቹን ፡ ፈቃድ ፡ አያ ስተጋባም ፡ በማለት ፡ በብርቱ ፡ ለመጠራጠር ፡ ይቻላል ። በቀን ፡ ሊኖሩ ፡ የሚገባቸ ውን ፡ የሥራ ፡ ሰዓቶች ፡ ቍጥር ፡ በሚወስኑት ፡ ደንቦችና ፡ በሳምንት ፡ ሊኖሩ ፡ የሚገ ባቸውን ፡ የሥራ ፡ ቀናት ፡ ቍጥር ፡ በሚወስኑት ፡ ደንቦች ፡ መካከል ፡ እንዳለው ፡ ቅርብ ግንኙነት ፡ ያላቸው ፡ ደንቦች ፡ በአንድነት ፡ መወሰድ ፡ አለባቸው ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል። ይኸውም ፡ ደንቦቹ ፡ በቀን ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ እና ፡ በሳምንት ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ በቀን ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ እና ፡ በሳምንት ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ተብለው ፡ መወሰድ ፡ አለባ ቸው ፡ ማለት ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ መሠረተ— አሳብ ፡ በሰፊው ፡ ተፈጻሚ ፡ ሊሆን ፡

34. አንቀጽ ፡ ፲ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፪ ፡ እና ፡ አንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ ሁኔታ ዎች ፡ ደረጃ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ።

35. በዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ የሚመደቡ ፡ ከሚመስሉ ፡ ጥቂቶች ፡ ደንቦች ፡ አንዱ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፩ ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ ለሠራተኞች ፡ መንፈሳዊ ፡ በዓሎችን ፡ አለደመ ወዝ ፡ እና ፡ ስድስት ፡ የሕዝብ ፡ በዓሎችን ፡ ከደመወዝ ፡ ጋር ፡ ይፈቅድላቸዋል ።

አይችልም ። ይህ ፡ መሠረተ — አሳብ ፡ እስከ ፡ ትክክለኛው ፡ የአስተሳሰብ ፡ ወሰኑ ፡
ድረስ ፡ ቢስፋፋ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፯፪ ፡ እና ፡ ስለሥራ ፡ ሁኔታ
ዎች ፡ ደረጃ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱትን ፡ ከመሻር ፡ የሚያድኑት ፡ ደን
ቦች ፡ በሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ላይ ፡ ሲፈጸሙ ፡ ምንም ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡
እንዳይኖራቸው ፡ ያደርጋቸዋል ። በአንድ ፡ በኩል ፡ በያንዳንዱ ፡ የሕግ ፡ ቅንጅት ፡ የኢ
ትዮጵያና ፡ የኤርትራ ፡ ማለታችን ፡ ነው ፡ ውስጥ ፡ ያለ፡ እያንዳንዱ ፡ መሠረታዊ ፡ የሥራ
ሁኔታ ፡ ደንብ ፡ በሌላው ፡ የሕግ ፡ ቅንጅት ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ ደንብ ፡ ጋር ፡ የተዛመደ
ነው ። ማንኛውም ፡ የሥራ ፡ ሁኔታ ፡ መሻሻል ፡ የአሠሪውን ፡ ወጪ ፡ ቢያንስ ፡ ለአ
ጭር ፡ ጊዜ ፡ ይጨምራል ። ይህም ፡ የሚሆነው ፡ በከፍተኛ ፡ ደሞዞች ፡ በኩል ፡ ብቻ ፡
ሳይሆን ፡ ከደመወዝ ፡ ጋር ፡ በሚሰጥ ፡ ረጅም ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ በአጭር ፡ የሥራ ፡
ሰዓቶች ፡ ወይም ፡ ለአደጋና ፡ ለሕመም ፡ በሚጨመሩ ፡ የአሠሪ ፡ አላፊነት ፡ በኩልም
ነው ። መሠረታውያን ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎችን ፡ የሚደነግጉ ፡ ደንቦች ፡ በሙሉ ፡ ይህን፡
የተጨመረውን ፡ ወጪ ፡ የሠራተኞችን ፡ ጥቅሞች ፡ ከመጠበቅ ፡ አስፈላጊነት ፡ ጋር
በማመዛዘን ፡ የተገኙ ፡ ውጤት ፡ ናቸው ፡ ወይም ፡ መሆን ፡ ይገባቸዋል ። በተግባር ፡
ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ ማናቸውንም ፡ ደንብ ፡ በ"ይበልጥ ፡ በተሻለ" ፡ ደንብ ፡ መተካት ፡
ሚዛኑን ፡ አዛብቶ ፡ ለሠራተኞች ፡ የበለጠ ፡ ጠቅላላ ፡ ጥቅሞችን ፡ ሲሰጥ ፡ በአሠሪ
ዎች ፡ ላይ ፡ የበለጠ ፡ ጠቅላላ ፡ ወጪን ፡ ያስከትልባቸዋል ። የሚዛኑም ፡ መዛባት ፡ በቀን
ውስጥ ፡ ስለተወሰኑ ፡ የሥራ ፡ ሰዓቶችና ፡ በሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ስለተወሰኑ ፡ የሥራ ፡
ቀኖች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደታተተው ፡ የፈጠራ ፡ ጉዳይ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ግልጽ
አይሆንም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጠባይ ፡ የሚዛኑን ፡ መዛባት ፡ እርግጠኛነት
አያሳንስም ።

ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ሦስት ፡ ዓይነት ፡ መፍትሔዎች ፡ ያሉ ፡ ይመስላል ። አንዱ ፡
መፍትሔ ፡ ከሌሎች ፡ ደንቦች ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ ሳንመለከት ፡ አንድ ፡ ደንብ
ለብቻው ፡ ሲወሰድ፡ለሠራተኞች ፡ በይበልጥ፡ከተሻለ ፡ የደንቡን ፡ ምትክነት ፡ መፍቀድ
ነው። ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የዕለታዊና ፡ የሳምንታዊ ፡ የሥራ ፡ ሰዓቶች ፡ የፈጠራ፡ጉዳይ
ይህ ፡ መፍትሔ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሊያመጣ ፡ የሚችለውን ፡ ውጤት ፡ ያሳያል ። ሁለ
ተኛው ፡ መፍትሔ ፡ የያንዳንዱ ፡ የሕግ ፡ ቅንጅት ፡ የኢትዮጵያና ፡ የኤርትራ ፡ መሠረ
ታዊ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡ የተዛመዱ ፡ መሆናቸውን ፡ ተገንዝቦ ፡ የኢ
ትዮጵያን ፡ ደንቦች ፡ በሙሉ ፡ ወይንም ፡ የኤርትራን ፡ ደንቦች ፡ በሙሉ ፡ መምረጥ ፡
ያሻል ። ይህን ፡ መፍትሔ ፡ ትክክለኛነቱ ፡ የማያጠራጥር ፡ ቢሆንም ፡ ስለሥራ ፡ ሁኔ
ታዎች ፡ ደረጃ ፡ ከወጣው ፡ አዋጅና ፡ ከሕግ ፡ ማስታወቂያ፡ ክፍል ፡ ቍ. ፫፻፯፪ ፡ የመጠ
በቂያ ፡ ደንቦች ፡ ጋር ፡ ማስታረቁ ፡ ቀላል ፡ ተግባር ፡ አይደለም ፡ ምክንያቱም ፡ እነዚህ ፡
የመጠበቂያ ፡ ደንቦች ፡ አንዳንድ ፡ የተለዩ ፡ የእነዚህ ፡ ሕግጋት ፡ ደንቦች ፡ በተሻሉ ፡
ሌሎች ፡ ደንቦች ፡ ሊተኩ ፡ ይችላሉ ፡ የሚል ፡ ሃሳብ ፡ ያዘሉ ፡ ስለሚመስሉ ፡ ነው ።[36]
በመጨረሻም ፡ በጣም ፡ የተቀራረበ ፡ ዝምድና ፡ ባላቸው ፡ ደንቦችና ፡ ራቅ ፡ ያለ ፡ ዝም
ድና ፡ ባላቸው ፡ ደንቦች ፡ መካከል ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ በግምት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ልዩ
ነት ፡ ለማምጣት ፡ ይቻላል ። ከመሻር ፡ ለሚያድኑት ፡ ደንቦች ፡ ተገቢው ፡ ትርጉም ፡
እንዲሰጥ ፡ ከተፈለገ ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

የዚህን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መወሳሰብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊነሳ ፡ የሚችል ፡ አንድ ፡
የተጨበጠ ፡ ፕሮብሌምን ፡ በመመልከት ፡ ለመረዳት ፡ ይቻላል ፡ ፕሮብሌሙም ፡ ተን

36. በአሠሪዎችና ፡ በሠራተኞች ፡ መካከል ፡ በሚደረጉ ፡ ስምምነቶች ፡ የተሻሉ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሲወሰኑ ፤

ታች ፡ ደንቦቹ ፡ ለማን ፡ በይበልጥ ፡ ያደላሉ ፡ ደግሞስ ፡ በምን ፡ ሁኔታዎች ? የሚሉ ትን ፡ ጥያቄዎች ፡ እንዲመልስ ፡ የሚያደርግ ፡ ይሆናል ። ከመሻር ፡ የሚያድኑትም ፡ ደንቦች ፡ "ለሠራተኞች" በይበልጥ ፡ የተሻሉ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ይጠቅሳሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሠራተኞች ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ስላልሆኑ ፡ ለአንድ ፡ ሠራተኛ ፡ በለጥ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ ደንብ ፡ ለሌላው ፡ ሠራተኛ ፡ አነስተኛ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ ለአንድ ፡ ሠራተኛ ፡ እንኳን ፡ ከሁለት ፡ ደንቦች ፡ መካ ከል ፡ በይበልጥ ፡ የሚሻለው ፡ እንደ ፡ አካባቢው ፡ ሁኔታ ፡ ሊለዋወጥ ፡ ይችላል ።

ይህ ፡ ችግር ፡ በሁለቱም ፡ ረገድ ፡ በሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡፴፮፡ እና ፡ በሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፸፪ ፡ አንቀጽ ፡ ፱ ፡ ጐልቶ ፡ ይታያል ። አንቀጽ ፡ ፴፮ ፡ ሠራተኞችን ፡ በሁለት ፡ ክፍሎች ፡ ይመድባል ፡ እነዚህም ፡ በወር ፡ ከመቶ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ የሚያገኙና ፡ በወር ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ወይንም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡የሚ ገኙ ፡ ናቸው ። በመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ ለአምስት ፡ አመታት ፡ ወይም ከዚያ ፡ በላይ ፡ ለአገለገሉ ፡ ሠራተኞች ፡ የሚሰጠው ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ የሶ ስት ፡ ወር ፡ ደሞዝና ፡ ከአምስት ፡ ዓመታት፡በላይ ፡ ላለው ፡ ለእያንዳንዱ፡ የአገልግሎት ዓመት ፡ የግማሽ ፡ ወር ፡ ደመወዝ ፡ ነው ፡ ከአምስት ፡ ዓመታት ፡ በታች ፡ ላገለገሉ ፡ ሠራተኞች ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ በተመጣጣኝ ፡ ሁኔታ ፡ ይቀነሳል ። ሁለተኛው፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ለሚመደቡ ፡ ሠራተኞች ፡ የሚሰጠው ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ለያ ንዳንዱ ፡ የሥራ ፡ ዓመት ፡ የወር ፡ ደሞዝ ፡ አንድ ፡ አራተኛውን ፡ ነው ። የሕግ ፡ ክፍል፡ ማስታወቂያ ፡ ቍ ፡ ፫፻፸፪ ፡ አንቀጽ ፡ ፱ ፡ በሠራተኞች ፡ መካከል ፡ በደመወዝ ፡ ብዛት ፡ መሠረት ፡ ልዩነት ፡ አይፈጥርም ። ለአንድ ፡ ዓመት ፡ ወይንም ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ለሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለአገለገለ ፡ ሠራተኛ ፡ የሚሰጠው ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ የሠራተኛው ፡መካ ከለኛ ፡ ዕለታዊ ፡ ደመወዝ ፡ ሰላሳ ፡ እጥፍ ፡ እና ፡ ከመጀመሪያው ፡ የሥራ ፡ ሰዓት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ላለው ፡ ለእያንዳንዱ ፡ የሥራ ፡ ዓመት ፡ ሃያ ፡ አምስት ፡ በመቶ ፡ ጭ ማሪ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ አንድ ፡ ሠራተኛ ፡ የአገልግሎት ፡ ዘመኑ ፡ ቢበዛም ፡ ከማዕከላዊ የዕለት ፡ ደመወዙ ፡ ከ፩፻፹፰ ፡ እጥፍ ፡ በላይ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ የለውም ።

ሁለቱ ፡ ደንቦች ፡ ሲነፃፀሩ ፡ በሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፸፪ ፡ ለ"መ ካከለኛ ፡ ዕለታዊ ፡ ደመወዝ" ፡ ስለሚሰጠው ፡ ፍቺ ፡ አንድ ፡ መሠረታዊ ፡ ችግር ፡ አለ ፤ የዚህ ፡ ሐረግ ፡ ትርጉም ፡ በአንድ ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጠው ፡ የሠራተኛው ፡ ደሞዝ ፡ በክፍለ ፡ ጊዜው ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ቀናት ፡ ጠቅላላ ፡ ቍጥር ፡ ሲካፈል ፡ ማለት ነው ፡ ወይስ ፡ በዚያ ፡ ክፍል ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጠው ፡ ደመወዝ ፡ በሥራ ፡ ቀናቱ ፡ ቍጥር ፡ ብቻ ፡ ሲካፈል ፡ ማለት ፡ ይሆን? ምናልባት ፡ የታሰበው ፡ ፍቺ ፡ የመጀመሪያው ፡ ይመ ስላል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በማናቸውም ፡ አተረጓጐም ፡ ጠቅላላ ፡ መደምደምያው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ነው ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፸፪ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ወይንም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በወር ፡ ለሚያገኙ ፡ ሠራተኞችና ፡ እንዲሁም ፡ ከተወሰኑ ፡ ዓመታት ፡ በታች ፡ ለተቀጠሩና ፡ በወር ፡ ከመቶ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ ለሚያገኙ ፡ ሠራተኞች ፡ የተሻሻለ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ይደነግጋል ፡ ስለ ፡ መካከለኛ ፡ ዕለታዊ ፡ ደመወዝ ፡ አተረጓ ጐም ፡ እዚህ ፡ በተሰጠው ፡ አስተያየት ፡ መሠረት ፡ የዓመታቱ ፡ ቍጥር ፡ በግምት ፡ ሁለት ፡ ነው ።[37] በወር ፡ ከመቶ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ ለሚያገኙና ፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ለአገለ

---

ይህንን ፡ ነገር ፡ በርግጥ ፡ አሰበውበታል ፡ (አቅደዋል) ፡ ይህንን ፡ የመሰሉ ፡ የግል ፡ስምምነቶች ፡ ከሕ ግጋት ፡ ጋር ፡ "ሕጋዊ ፡ ወሰኖች" ተብለው ፡ ከመሻር ፡ በሚያድኑት ፡ ደንቦች ፡ ተመድበዋል ።

37 . በሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ ከአምስት ፡ የአገልግሎት ፡ ዓመታት ፡ በታች ፡ ያለው ፡

ገሉ ፡ ሠራተኞች ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ የተሻለ ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ፡ ይደነግጋል ። ስለዚህ ፡ የሠራተኞች ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፮ ፡ ወይንም ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍ ፡ ፫፻፪ ፡ ለሠራተኞች ፡ በይበልጥ ፡ ይሻላል ፡ ለማለት፡ የሚቻለው ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከታቸውን ፡ ሠራተኞች ፡ ከማስተዋል ፡ በኋላ ፡ ነው ።

ሁለቱም ፡ ደንቦች ፡ በምን ፡ ሁኔታ ፡ የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ ይፈጥራሉ ። የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ደንቦች ፡ ሳይሟሉ ፡ ከሥራ ፡ የሚሰናበት ፡ ሠራተኛ ፡ በሕግ ፡ ስለተ ወሰነው ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ልክ ፡ የሚጠበብበት ፡ ምክንያት ፡ የለውም ። የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፪ ፡ ምናልባት ፡ ለአብዛኞቹ፡ ሠራተኞች ፡ የተሻሻለ ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ቢደነግግም ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ለሠራተኞች ፡ በአያሌ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታዎች ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ እንዲሰጥ ፡ ያዛል ።

የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ከሁለት ፡ ሁኔታዎች ፡ በስተቀር ፡ በሌሎች ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ እንዲሰጥ ፡ ይደነግጋል ። የተጠበቁት ፡ ሁኔታዎችም ፡ የሠራተኛው ፡ በአንቀጽ ፡ ፴፫ ፡ ሥር ፡ በተዘረዘሩት ፡ ጥፋቶች ፡ ምክንያት ፡ ከሥራ ፡ መባረርና ፡ የሠራተኛው ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ የሥራ ፡ ውሉን ፡ ማቆም ፡ ናቸው ።

የመጀመሪያው ፡ የተጠበቀ ፡ ሁኔታ ፡ በሁሉም ፡ ሠራተኞች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። ሆኖም ፡ ሁለተኛው ፡ በወር ፡ ከመቶ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ በሚያገኙ ፡ ቢያንስ ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ባገለገሉት ፡ ሠራተኞች ፡ ወይንም ፡ ቢያንስ ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ ባገለገሉት ፡ ሌሎች ፡ ሠራተኞች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ፡ እነዚህ ፡ ሠራተኞች ፡ አሠሪው ፡ ሳይሆን ፡ ራሳቸው ፡ የሥራውን ፡ ውል ፡ ሲያቆሙ ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ የማግኘት ፡ መብት ፡ አላቸው ።

የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፪ ፡ ተግባሩን ፡ የሚፈጽመው ፡ ከተቃራኒው ፡ አቅጣጫ ፡ ነው ፡ ሠራተኛው ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ የማያገኙባቸውን ፡ ሁኔታዎችን ፡ በመዘርዘር ፡ ፈንታ ፡ ሠራተኛው ፡ ይህን ፡ ክፍያ ፡ የሚያገኝበትን ፡ አንድ ፡ ሁኔታ ፡ ይጠቅሳል ፡ ይህም ፡ አሠሪው ፡ አለበቂ ፡ ምክንያት ፡ ሠራተኛውን ፡ ከሥራ ፡ በሚያሰናብትበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ይህን ፡ ሁኔታ ፡ ሠራተኛው ፡ በሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ከሚያገኝባቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ ጋር ፡ ስናነፃፅር ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፪ ፡ ለሠራተኞች ፡ በሁለት ፡ መንገዶች ፡ አነስ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ ይመስላል ። በመጀመሪያ ፡ በሕግ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ሠራተኛ ፡ ሥራውን ፡ ራሱ ፡ ካቆመ ፡ የስራ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ፈጽሞ ፡ አያገኝም ። ሁለተኛ ፡ ሠራተኛው ፡ ጥፋት ፡ ሳይገኝበት ፡ በበቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራ ፡ የሚሰናበትበት ፡ ሁለት ፡ ሁኔታዎች ፡ አሉ ። እነዚህም ፡ ሁኔታዎች ፡ "ውሉ ፡ እንዲታደስ ፡ ወይም ፡ እንዲራዘም ፡ ባሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ለአእምሮ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ባልተገኘ ፡ ጊዜ" እና ፡ "ሠራተኛው ፡ የሚሠ

ከመቶ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ የሚያገኝ ፡ ሠራተኛ ፡ ለያንዳንዱ ፡ የአገልግሎት ፡ ዓመት ፡ የወር ፡ ደመወዙ ፡ ሶስት ፡ አምስተኛ ፡ የሚያህል ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ። አንድ ፡የአገልግሎት ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ላለው ፡ ሠራተኛ ፤ ይህ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፪ ፡ ከሚደነገገው ፡ በታች ፡ ነው ፡ (የወር ፡ ደሞዝ ፡ ሦስት ፡ አምስተኛ ፡ ከደመወዝ ፡ ጋር ፡ ሲነፃፀር) ፤ ሁለት ፡ የአገልግሎት ፡ ዓመት ፡ ላለው ፡ ሠራተኛ ፡ ሁለቱም ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ እኩል ፡ ናቸው ፡ (አንድና ፡ አንድ፡ አምስተኛ ፡ የወር ፡ ደሞዝ ፡ ከአንድና ፡ ሩብ ፡ የወር ፡ ደሞዝ ፡ ጋር ፡ ሲነፃፀር) ፤ እና ፡ ሁለተኛው ፡ የአገልግሎት ፡ ዓመት ፡ ከተፈጸመ ፡ ጥቂት ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ የሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ የደነገገው ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ይበልጣል ።

ራው ፡ ሥራ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ቀሪ ፡ የተደረገ ፡ እንደሆነ"[38] ፡ ናቸው ። በሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ሠራተኛ፡ በሁለቱም ፡ ሁኔታዎች ፡ የሥራ ፡ ስን ብት ፡ ክፍያ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ይመስላል ።[39]

አሁን ፡ በይበልጥ ፡ የተሻለ ፡ የሚለው ፡ ደረጃ ፡ በዚህ ፡ በጥቅሞችና ፡ ጉዳቶች ፡ ቅይጥ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዲኖረው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ አለበት ? አንዱ ፡ መንገድ ፡ ከያንዳንድ ፡ የበለጠውን ፡ መውሰድ ፡ ነው ፤ ለዚህም ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ይገባል ፡ የሚለውን ፡ ጥያቄና ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ በይበልጥ ፡ የሚሻል ፡ ከሆነ ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ብዛትን ፡ እንዲወስን ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቊጥር ፡ ፫፻፪ ፡ በይበልጥ ፡ የሚሻል ፡ ከሆነ ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ብዛትን ፡ እንዲወስን ፡ ማድረግ ፡ ነው። ሆኖም ፡ ይህ ፡ መንገድ ፡ አንድ ተዛማጅ ፡ ደንብ ፡ ከሌላ ፡ ደንብ ፡ መነጠሉን ፡ ሳይሆን ፡ ከነጠላ ፡ ደንቦች ፡ እንኳን ፡ እጅግ፡በጣም፡የሚሻሉትን፡ክፍሎች፡መርጦ፡በማዋሐድ፡ ከአዋጁ፡ወይም ፡ ከሕግ ፡ ክፍል፡ ማስታወቂያው ፡ ደንብ ፡ ጋር ፡ የማይመሳሰል ፡ አንድ ፡ የተዋሐደ ፡ ደንብ ፡ መፍጠርን፡ ይጠይቃል ። ይህ ፡ ዘዴ ፡ በግልጽ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ መገባቱንና ፡ ለያንዳንዱ ፡ የሠራተኛ ፡ ክፍል ፡ የሚሰጠውን ፡ የሥራ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ የሚነኩ ፡ ጥያቄዎች ፡ በተነጣጠሉ ፡ ደንቦች ፡ እንዲወሰኑ ፡ ማድረግ ይቻል ፡ ነበር ። የዚህ ፡ አለመደረግ ፡ እንደ ፡ ቅጽ ፡ (ፎርም) ፡ ፕሮብሌም ፡ ሊቆጠር ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ዕለታዊና ፡ ሳምንታዊ ፡ የሥራ ፡ ሰዓቶችን ፡ በተመለከተው ፡ የፈጠራ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ የተፈጠረው ፡ የአርቃቂዎቹንና ፡ የአጋጊዎቹን ፡ ፈቃድ ፡ የሚመለከተው ፡ ጥርጣሬ ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ መገባትንና ፡ ብዛትን ፡ በሚ መለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥም ፡ ሊፈጠር ይችላል ።

ሁለተኛው ፡ ምርጫ ፡ የያንዳንዱን ፡ ደንብ ፡ ጥቅም ፡ እና ፡ ጉዳት ፡ አመዛዝኖ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ሌላው ፡ በሙሉ ፡ ቢወሰድ ፡ በይበልጥ ፡ ይሻላል ፡ ብሎ ፡ መወሰን ፡ ነው ። የዚህ ፡ ምርጫ ፡ ችግሩ ፡ የመለኪያ ፡ ደረጃ ፡ እጦት ፡ ነው ። የስምንት ፡ የሥራ ፡ ሰዓቶች ፡ ቀንና ፡ የስድስት ፡ የሥራ ፡ ቀናት ፡ ሳምንትን ፡ ከዘጠኝ ፡ የሥራ ፡ ሰዓቶች ቀንና ፡ ከአምስት ፡ የሥራ ፡ ቀናት ፡ ሳምንት ፡ ጋር ፡ ማነፃፀር ፡ አስቸጋሪ ፡ አይደለም ፡ ምክንያቱም ፡ እያንዳንዱ ፡ ሊለካ ፡ የሚቻልበት ፡ ጉልሕ ፡ የሆነ ፡ ደረጃ ፡ ስላለው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ጠቅላላ ፡ የሰዓት ፡ ቊጥር ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ለአንዳንድ ፡ ሠራተኞች ፡ የተሻለው ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ለሌሎች ፡ ሠራተኞች ፡ ከሚሰጠው ፡ የተሻለ ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ጋርና በሌላው ፡ በኩል ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያዎች ፡ ከሚሰጡባቸው ፡ በዛ ፡ ካሉት ፡ ጉዳ ዮች ፡ ጋር ፡ ተመዛዝኖ ፡ የሚለካበት ፡ ጉልሕ ፡ የሆነ ፡ ደረጃ ፡ የለም ። ይሠራባቸዋል ፡ ተብሎ ፡ የሚታመንባቸውም ፡ ደረጃዎች ፡ ለምሳሌ ፡ ለሁሉም ፡ ሠራተኞች ፡ የሚሰጥ፡

38. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፪ሺ፭፻፳፮ ።

39. በሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቊጥር ፡ ፫፻፪ ፡ መሠረት ፡ አለኝ ፡ የሚለውን ፡ መብት ፡ በአሠሪው ፡ ላይ፡ ለማስፈጸም ፡ በሞከረው ፡ ከአብዛኞቹ ፡ አንዱ ፡ በሆነው ፡ ሠራተኛ ፡ ላይ ፡ መፈረዱ ፡ በዚህ ፡ በፈጠራው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ የሕግ ፡ አተረጓጐም ፡ ላይ ፡ ሊመሠረት ፡ ወይም ፡ ላይመሠረት ፡ ይችላል ፡ ሁለት ጥያቄዎች ፡ ሊቀርቡ ፡ ይችላሉ ፡- በመጀመሪያ ፤ በደንቦች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ እና ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በነጠላ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፤ አንዳንድ ፡ ሠራተኞች ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ የአንቀጽ ፡ ፴፯ን ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ጥቅሞች ፡ ሲያገኙ ፡ ሌሎች ፡ ሠራተኞች ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቊጥር ፡ ፫፻፪ ፡ የአንቀጽ ፡ ፺፩ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ጥቅሞች ፡ እንዲያገኙ ፡ ተደርገው፡ ደንቦቹ ፡ ሊከፋፈሉ ፡ ይችላሉ ፡ ወይ ? ሁለተኛ ፡ ደንቦቹን ፡ መከፋፈል ፡ ከተቻለ ፡ የሕግ፡ ክፍል ፡ ማስታ ወቂያ ፡ ቊጥር ፡ ፫፻፪ ፡ በይበልጥ ፡ የተሻለውን ፡ የሚለውን ፡ የአብዛኛዎቹን ፡ ሠራተኞች ፡ ውሳኔ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይስማማበታል ፡ ወይ ?

የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ምንም ፡ የሥራ ፡ ክፍያ ፡ ባለመኖሩ ፡ ሲቀነስ ፡ አሁን ፡ ካለን የፍሬ ፡ ነገር ፡ ዝርዝር ፡ ጋር ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውሉ ፡ አይችሉም ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በኩልም ፡ ለሕጋዊ ፡ አፈጻጸም ፡ ምቹ ፡ አይደሉም ።

በነዚህ ፡ ሁለት ፡ ምርጫዎች ፡ የሚነሱት ፡ ሕጋዊና ፡ ተግባራዊ ፡ ችግሮች ፡ ሲመረመሩ ፡ ችግሮቹን ፡ በቦታ ፡ ምርጫ ፡ ለማጥፋት ፡ ያጓጓ ፡ ይሆናል ፡ ይኸውም ፡ በያንዳንዱ ፡ ድርጅት ፡ ያሉት ፡ ሠራተኞች ፡ ሻል ፡ ብሎ ፡ የሚታያቸውን ፡ ደንብ፡ ራሳቸው ፡ እንዲወስኑ ፡ ለመፍቀድ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሆኖም ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ዘዴ ፡ ተግባራዊ ፡ ጥቅም ፡ ቢኖረውም ፡ ሕጋዊነቱ ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ። ከሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፮ን ፡ ከሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍ ፡ ፻፶፪ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፮ን ፡ እና ፡ ከመሻር ፡ የሚያድኑትን፡ደንቦች፡ማዋሐድ ለኤርትራ፡ሠራተኞች፡የተወሰኑ ፡የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ መብቶችን ፡ ይሰጣል ። ከዚህ በፊት ፡ የተገለጸው ፡ አስተያየት ፡ እንደሚያስረዳው ፡ እነዚህ ፡ መብቶች ፡ የትኞቹ ፡ እንደሆኑ ፡ መወሰን ፡ ቀላል ፡ አይደለም ፤ ግን ፡ የአተረጓጐም ፡ ችግሮች ፡ የመተርጐምና ፡ በትርጉሙ ፡ መሠረት ፡ ውሳኔ ፡ የመስጠት ፡ ግዴታን ፡ ጉዳይ ፡ ከሚመለከተው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ አያወርድም ። ቀጥሎም ፡ በአንድ ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ሠራተኞች ፡ የሕግ ፡ ማስታወቂያ ፡ ክፍል ፡ ቍ. ፻፶፪ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፮ ፡ ተፈጻሚ፡ እንዲሆን ፡ ወሰኑ ፡ እንበል ። ከሠራተኞቹ ፡ ጥቂቶቹ ፡ ማለት ፡ ከፍተኛ ፡ የወር ፡ ደሞዝ እና ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ የአገልግሎት ፡ ዘመን ፡ ያላቸው ፡ ሳይስማሙ ፡ ይቀራሉ ። ከነዚህ ፡ ከጥቂቶቹ ፡ ሠራተኞች ፡ አንዱ ፡ ከሥራ ፡ ተወግዶ ፡ በሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ፡ መሠረት ፡ የሚገባውን ፡ የሥራ ፡ ስንብት ፡ ክፍያ ፡ ለማግኘት ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲሄድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አብዛኞቹ ፡ ሠራተኞች ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፻፶፪ን ፡ መርጠዋል ፡ በማለት ፡ ክሱን ፡ ቢያሰናብት ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተግባር ፡ ትክክል ፡ ይሆናል ፡ ወይ ? ትክክል ፡ የማይሆን ፡ ይመስላል ። ይልቅስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሠራተኛው ፡ እንደሚከራከረው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተገቢዎቹ ፡ ደንቦች ፡ ትርጉም ፡ መሠረት ፡ የሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ መዳኘቱን ፡ እንዲወስን ፡ ይገደዳል ። ፍርድ፡ ቤቱ ፡ የሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ይዳኛል ፡ ካለም ፡ የአብዛኞቹ ፡ ሠራተኞች ፡ ውሳኔ ፡ ሳይታይ ፡ ሠራተኛው ፡ ፍርድ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

የሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ መሠረታዊ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ደንቦች ሁሉ ፡ አልተሻሩም ፡ ብሎ ፡ ለመደምደም ፡ ሁለተኛው ፡ ምክንያት ፡ ከነሱ ፡ መካከል ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፻፶፪ ፡ ወይም ፡ ስለሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ደረጃ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ያልጠቀሱአቸውን ፡ አንዳንድ ፡ መሠረታዊ ፡ ደረጃዎችን ፡ ስለሚወስኑ ፡ ነው ።[40] እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ በቀጥታ ፡ የሚመስሉአቸው ፡ ደንቦች ፡ ስለሌሉ ፡ ከሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፻፶፪ ፡ እና ፡ ስለሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ከወጣው ፡ አዋጅ ፡ ተነፃፃሪ ፡ ደንቦች ፡ የግድ ፡ ለሠራተኞች ፡ የተሻሉ ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግጋት ፡ የመሻሪያ ፡ ደንቦች ፡ ስለማይመለከታቸው ፡ ለሠራተኞች ፡ የተሻሉ ፡ ናቸው ፡ የሚል ፡ ምክንያት ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

## ማጠቃለያ ።

የ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኤርትራ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅን ፡ አሁን ፡ ያለውን ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ ስንመራመር ፡ የአዋጁ ፡ ታሪክ ፡ በሦስት ፡ ክፍሎች ፡ ይመደባል ። መጀ

40. ለምሳሌ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያውም ፡ ሆነ ፡ አዋጁ ፡ ከሥራ ፡ ጋር ፡ በተያያዘ ፡ ሕመም ፡ ወይም፡ አደጋ ፡ የአሠሪውን ፡ አላፊነት ፡ አይመለከቱም ።

መሪያው ፡ ሕጉ ፡ ከወጣ ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ ፌዴራሲዮኑ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ክፍል ፡ ጊዜ ፡ ሕጉ ፡ ሊሻር ፡ ወይም ፡ ሊሻሻል ፡ ይችል ፡ የነበረው ፡ ከሕጉ ፡ በኋላ ፡ በሚወጡት ፡ የፌዴራል ፡ ወይም ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ ነበር ። ይህን ፡ የመሰለ ፡ የሠራተኛ ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ የሚመለከታቸውን ፡ ጉዳዮች የሚመለከት ፡ ሕግ ፡ ያልነበረ ፡ ስለሚመስል ፡ አዋጁ ፡ እስከ ፡ ፌዴራሲዮን ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ በሙሉ ፡ ጽኑ ፡ ሆኖ ፡ ቆየ ።

የአዋጁ ፡ ታሪክ ፡ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ የፌዴራሲዮኑ ፡ ፍጻሜ ፡ ነው ። የፌዴራሲዮኑ ፡ ፍጻሜ ፡ በሁሉም ፡ የኤርትራ ፡ ሕግጋት ፡ ላይ ፡ የመሻር ፡ ውጤትን ፡ ሊያስከትል ፡ ይችል ፡ ነበር ፡ ደግሞም ፡ ፌዴራሲዮኑን ፡ የሻረው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ትዕዛዝ ፡ ደንቦች ፡ በጠባቡ ፡ ተተርጉመው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ከፌዴራሲዮኑ ፡ ደንቦች ፡ጸንተው ፡ የሚቀሩት ፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ በሆኑ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ደንቦቹ ፡ የኤርትራን ፡ ሕግጋት ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ከጥቂቶች ፡ በስተቀር ፡ ሌሎቹን ፡ በሙሉ ፡ ከመሻር ፡ እንዲያድኑ ፡ ተደርገው ፡ በሰፊው ፡ ተተርጉመዋል ፡ የሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅም ፡ ከፌዴራሲዮኑ ፡ ፍጻሜ ፡ ወዲህ ፡ ሕጋዊ ፡ ጽኑነቱ ፡ ቀጥሏል ።

ከፌዴራሲዮኑ ፡ ፍጻሜ ፡ ወዲህ ፡ የሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ የሚመለከታቸውን ፡ ጉዳዮች ፡ የሚመለከቱ ፡ አራት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግጋት ፡ ወጥተዋል ። እነዚህም ፡ ሕግጋት ፡ በሠራተኛው ፡ አቀጣጠር ፡ አዋጅ ፡ ላይ ፡ ያስከተሉት ፡ ውጤት ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፡

፩/ ሦስት ፡ ዓይነት ፡ ደንቦች ፡ የተሻሩ ፡ ይመስላሉ ፤

ሀ/ የሠራተኛ ፡ ማኅበሮችንና ፡ የአሠሪዎችን ፡ ማኅበሮች ፡ የሚመለከቱት ፡ ደንቦች ፤ እነዚህም ፡ ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣው ፡ ድንጋጌ ፡ ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ተብሎ፡ እንደገና ፡ በ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ፡ም፡በወጣ፡ጊዜ ፡ የተሻሩ ፡ ይመስላሉ፤

ለ/ ስለሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ መቆጣጠሪያ ፡ የሚመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ እነዚህም ፡ በከፊል ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ መቆጣጠሪያ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በወጣው ፡ ትዕዛዝና ፡ በከፊል ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ደረጃ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ የተሻሩ ፡ ይመስላሉ ፡

ሐ/ እንደ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፪ ፡ እና ፡ ስለሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ደረጃ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ለሠራተኞች ፡ ተመሳሳይ ፡ ደንቦች ፡ የተሻለ ፡ ጥቅም ፡ የማይሰጡ ፡ መሠረታዊ፡ የሥራ ፡ ሁኔታ ፡ ደንቦች ፡ እነዚህም ፡ የሕጉ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመውጣቱና ፡ አዋጁ ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመውጣቱ ፡ የተሻሩ ፡ ይመስላሉ ።

፪/ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ደንቦች ፡ ያልተሻሩ ፡ ይመስላሉ ፡

ሀ/ ከሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፪ ፡ ወይም ፡ ስለሥራ ሁኔታዎች ፡ ደረጃ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ውስጥ ፡ ተነፃፃሪ ፡ የሌላቸው ፡ መሠረታዊ ፡ የሥራ፡ ሁኔታዎች ፡ ደንቦች ፤

ለ/ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፪ ፡ ወይም ፡ ስለሥራ ፡ ሁኔታዎች ፡ ደረጃ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ያልጠቀሱዋቸው ፡ መሠረታዊ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታዎችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ።